# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# የቤተመቅደስ መሪው ወደ ኢየሱስ መጣ

ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Maillot; Sarah S.

Alastair Paterson

የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2020 Bible for Children, Inc.
**ፈቃድ**፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ኢየሱስ አንድ ቀን ወደ ቤተመቅደስ ሲሄድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቤት ሲያዋርዱ አገኘ። እነርሱም በቤተመቅደስ ውስጥ እንስሳትን እየሸጡ ገንዘብ ይለዋወጡ ነበር።



ከአውታርም ጅራፍ ሰራ። ኢየሱስም ነጋዴዎቹን ከቤተ መቅደስ አስወጣቸው። "እነዚህን ነገሮች ከዚህ አውጡ" ብሎም አዘዛቸው። ኢየሱስ የአባቱን ቤት ይወድ ነበርና "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት" ብሎ ተቆጣ።





መሪዎቹ ኢየሱስ ቤተመቅደስን የማንፃት መብት እንዳለው ለማሳየት ምልክት እንዲደረግላቸው ጠየቁ። ኢየሱስም "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ውስጥ አነሳዋለሁ" ሲል መለሰላቸው። የማይቻል ነው! ቤተ መቅደሱን ለመገንባት አርባ ስድስት ዓመታት

ኢየሱስ ግን የተናገረው
ስለ ሰውነታቸው ነበረ። እንደ
ቤተመቅደስ, ሰውነታችን
የእግዚአብሔር መኖሪያ
ስፍራ ነው። ኢየሱስ
በመስቀል ላይ ቢሞት
እንኳን በሦስተኛው
ቀን እግዚአብሔር
ከሞት እንደሚነሣው
ያውቅ ነበር።





ምሽት ላይ ከቤተመቅደስ መሪዎች አንዱ ወደ ኢየሱስ መጣ። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን በተዓምራቶቹ ያውቃል። ኒቆዲሞስ ስለ እግዚአብሔር የበለጠ ለመማር ወደ ኢየሱስ መጣ።



ኢየሱስ ኒቆዲሞስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ዳግመኛ መወለድ እንደሚያስፈልጋቸው ነገረው። ኒቆዲሞስ ግን አልተረዳውም ነበር። አንድ ትልቅ ሰው እንደገና እንደ ሕፃን እንዴት ሊወለድ ይችላል? ከዚህም በላይ ሃይማኖተኛ ነበር። ይህ በቂ አልነበረም ማለት ነው?



ኢየሱስ "ከመንፈስ
የተወለደ መንፈስ
ነው" ሲል አስረዳ።
"የእግዚአብሔር
መንፈስ እንደ
ነፋስ ነው። ሰዎች
ነፋስን አያዩም
ወይም
አያስተውሉም።
ነገር ግን ሲነፍስ
ብቻ ያዩታል።"



ኢየሱስም ከረጅም ጊዜያት በፊት የእስራኤላውያን ልጆች በሙሴ ላይ ሲያማርሩ እንደነበር ለኒቆዲሞስ አስታወሰው። "ምግብ የለንም፣ ውኃም የለምእግዚአብሔር የሚሰጠንንም ዳቦ አንፈልግም" ብለው ጮኹ።

የሕዝቡ ኃጢአት እግዚአብሔርን አስቆጣው። በመካከላቸውም እሳት የሚተፉ እባብ ላከባቸው። እባቦቹ ሰዎቹን ነደፏ ቸው ብዙዎችም ሞቱ።



ህዝቡም "ኃጢአትን
ሠርተናል እነዚህን እባቦች
እንዲያጠፋልን ወደ እግዚአብሔር
ፀልይ።" ብለው ሙሴን ለመኑት።
ስለዚህ ሙሴ ለእነሱ ጸለየላቸው።
እግዚአብሔር ግን
እባቦችን አላጠፋቸውም ነበር።



እግዚአብሔርም ሙሴን እሳትን
የሚተፋ እባብ እንዲሠራና
በእንጬት ላይ እንዲሰቅለው
ነገረው። "በእባቦቹ የተነከሰ
ሁሉም ሰው የተሰቀለውን እባብ
ባየ ጊዜ በሕይወት ይኖራል"
በማለት ቃል ገባላቸው። ሙሴ
የናስ እባብ ሠራ እናም እባቡ
የተመለከቱ ሰዎች ተፈወሱ።





ኢየሱስም ኒቆዲሞስን, የሰው
ልጅ እንደ ናስ እባብ ከፍ ከፍ
እንዲል እንዳዘዘው ነገረው።
ኢየሱስ ለኃጢአተኞች
ስለሚሞትበት
ስለ መስቀል
መናገሩ ነበር።


ኢየሱስም አለ "በእርሱ
የሚያምን ሁሉ የዘላለም
ሕይወት እንዲኖረው እንጂ
እንዳይጠፋ እግዚአብሔር
አንድያ ልጁን እስኪሰጥ
ድረስ ዓለሙን እንዲሁ
ወዶአልና።"


ይህ ማለት
በኢየሱስ የሚያምነው
በእግዚአብሔር
ቤተሰብ ውስጥ
ተወልዷል
ማለት ነው።

ምናልባት ኒቆዲሞስ በዚያ ምሽት የኢየሱስ ደቀ መዝሙር አልሆነም። ሆኖም ግን ከዓመታት በኋላ,
ኒቆዲሞስ የተሰቀለው የእግዚአብሔር ልጅን እንዲቀበር በማገዝ ኢየሱስን እንደሚወደድና እንደሚያምን አሳይቷል።



ከዚህም በኋላ ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ሰሜን ለመጓዝ አሰቡ። ሌሎች ሰዎች ስለ አምላክ መንግሥት መስማት ያስፈልጋቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በናዝሬቱ በኢየሱስ እንዲያምኑ እድል አግኝተዋል።



# የቤተመቅደስ መሪው ወደ ኢየሱስ መጣ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዮሐንስ 2-3, ዘኁልቁ 21

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።